የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETEE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፪
አዲስ አበባ ታህሳስ ፩ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No.2
ADDIS ABABA 10th December 2013

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፲፪/፪ሺ፮ ዓ.ም

ለአዲስ አበባ - አዳማ የፍጥነት መንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር እንዲሁም ለአዲስ አበባ - አዳማ የፍጥነት መንገድ ክፍል ሁለት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከቻይና የኤክስፖርት - ኢምፖርት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ............ገጽ ፯ሺ፩፻፲፫

**CONTENTS**

**Proclamation No. 812/2013**

**Export - Import Bank of China Loan Agreement Periods Additional Loan for Addis Ababa Adama Toll Motorway Design and Build and a Loan for Addis Ababa Toll Motorway Phase II Project Ratification Proclamation ....... Page 7113**

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፲፪/፪ሺ፮

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና የኤክስፖርት -ኢምፖርት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለአዲስ አበባ - አዳማ የፍጥነት መንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ፩፻፵፫ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (አንድ መቶ አርባ ሦስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) እንዲሁም ለአዲስ አበባ - አዳማ የፍጥነት መንገድ ክፍልሁለት - ከለቡ - አቃቂ - የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ ካለው የቀለበት መንገድ ጋር ለሚያገናኘው ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፩፻፺ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (አንድ መቶ ዘጠና ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና የኤክስፖርት - ኢምፖርት ባንክ መካከል እ.አ.አ. ሴፕቴምበር ፲ ቀን ፪ሺ፲፫ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ህዳር ፲፱ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION No. 812/2013.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE EXPORT-IMPORT BANK OF CHINA

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export Import Bank of China provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia additional loan in an amount not exceeding USD 143,000,000 (one hundred forty three million United States Dollars) for financing the Addis Ababa Adama Toll Motorway Design and Build Road Projed and USD 190,000,000 (one hundred ninety million United States Dollars) for financing the Design and Build of Addis Ababa – Adma Toll Motorway Phase II, Lebu – Akaki – Information Technology Park Outer Ring Road Project was signed in Addis Ababa on the 10th day of September, 2013;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 28th day of November, 2013;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit Gazette P.O.box 80,001

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለአዲስ አበባ - አዳማ የፍጥነት መንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር እንዲሁም ለአዲስ አበባ - አዳማ የፍጥነት መንገድ ክፍል ሁለት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከቻይና የኤክስፖርት - ኢምፖርት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፲፪/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና የኤክስፖርት - ኢምፖርት ባንክ መካከል እ.አ.አ. ሰፕቴምበር ፲ ቀን ፪ሺ፲፫ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር PBC No. 2013(35) Total No. (279) 1420303052013211786 የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ስልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፫፻፴፫ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (ሦስት መቶ ሠላሳ ሦስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፩ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**
**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Export Import Bank of China Loan Agreement Periods Additional Loan for Addis Ababa Adama Toll Motorway Design and Build and a Loan for Addis Ababa Toll Motorway Phase II Project Ratification Proclamation No. 812/2013".

## 2. Ratification of the Agreement

The Loan Agreement No. 2013(35) Total No. (279) 1420303052013211786 signed in Addis Ababa on the 10th day of September, 2013 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export – Import Bank of China is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 333,000,000 USD (three hundred thirty three million United States Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 10th day of December, 2013.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**